# የዳዊት ካርታ



## አሁን ስለእስራኤልም ሆነ ይሁዲ መሆን ስለሚሰጠን ስሜት ማውራት ቀላል ሆኗል

አጋቾ የትምህርት መሳሪያ – የካቲት 2025

**የዳዊት ካርታዎች** - **ስለይሁዲ ማንነት፣ ስለእስራኤል፣ እንዲሁም ስለ ይሁዲ ሕዝባዊነት ትርጉም ያለው ውይይት ማድረግ ለሚፈልጉ ይሁዲ እና እስራኤላዊ መምህራን የተዘጋጀ ስሜት ቀስቃሽ አጋዥ የትምህርት መሳሪያ ካርታዎች ስብስብ ነው።**

**የዴቪድ ካርታዎች** ስብስብ፣ ይሁዲ መምህራን በሚከተሉት ሶስት ቁልፍ ጥያቄዎች ላይ ሐቀኛ እና ትርጉም ያላቸውን ውይይቶች ለመምራት እንዲያስችላቸው የተዘጋጀ ነው፡-

1. በአሁኑ ወቅት የይሁዲ ማንነቴን እንዴት እመለከተዋለሁ?
2. ከእስራኤል ጋር ያለኝ ግንኙነት ምን ይመስላል?
3. በዓለም ላይ ከሚገኙ ሌሎች ይሁዲዎች ጋር ያለኝን ግላዊ ትስስር እንዴት አየዋለሁ?

የዴቪድ ካርታዎች ከዚህ ጋር አባሪ በሆኑት የፈጠራ ንድፎች አማካኝነት መምህራን እና ተሳታፊዎች ውስብስብ በሆኑ እና አልፎ አልፎም ጥንቃቄን በሚፈልጉ ጥያቄዎች ዙሪያ ቅን እና ግልጽነትን የተሞላ ውይይት እንዲያደርጉ ለማስቻል አጋጣሚዎችን ይፈጥራሉ። የዳዊት ካርታዎች በማንኛውም የዕድሜ ክልል የሚገኙ (ከታዳጊዎች አንስቶ እስከ አዋቂዎች) ተሳታፊዎች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ትርጉም ያለው እና ግልጽነት የተሞላ ውይይት እንዳያደርጉ የሚከለክሏቸውን ተግዳሮቶች በተሳካ መልኩ ያስወግዳሉ።

ይህንን አጋዥ የትምህርት መሳሪያ ያዘጋጀው **ዮኒ አሎን** ሲሆን ንድፉን የሰራችው ደግሞ እስራኤላዊቷ አርቲስት **ሳፒር ዊነር አቪቭ** ናት። የይሁዲ ለእስራኤል ኤጀንሲ (JAFI) እና የእስራኤልን እና የዓለም ይሁዲዎችን ትስስር ማጠናከሪያ ብሄራዊ ጥምረት - AMI በጋራ ያዘጋጁት ፕሮግራም ነው።

THE JEWISH AGENCY FOR ISRAEL הסוכנות היהודית לארץ ישראל

The National Alliance Strengthening Israelis' Connection to World Jewry המנהלת הלאומית לקשרי ישראלים והתפוצות

AMI עמי

## በምን መልኩ ይሰራል?

ተሳታፊዎች **በእነርሱ እና ከፊት ለፊታቸው ባሉት ንድፎች በተወከለው የዳዊት ኮከብ (ማገን ዳዊት) መካከል ያለውን ዝምድና በምናባቸው እንዲያስቡ** ይጠየቃሉ። የዳዊት ኮከብ፣ ይሁዲነትን፣ እስራኤልን፣ የእስራኤል ይሁዲዎችን እንዲሁም የዓለም የይሁዲ ማህበረሰብን ለመወከል ሊጠቅም ይችላል። መምህሩ በማንኛውም ጊዜ ማተኮር የፈለገበትን ርዕሰ-ጉዳይ ተከትሎ የዳዊት ኮከብ በዚያ ውይይት ላይ የሚወክለውን ርዕሰ-ጉዳይ ሊወስን ይችላል።

**ካርታዎቹ ሰስት ዋና ዋና ግንኙነቶችን ለመግለጽ ይጠቅማሉ፡-**

- **ይሁዲነት እና እኔ**
- **እስራኤል እና እኔ**
- **የዓለም ይሁዲነት / የእስራኤል ይሁዲዎች እና እኔ**

### የአጠቃቀም ምክር

1. ከውይይቱ የሚጠበቁትን ነገሮች አስቀድሞ መወሰን።
2. በየትኛው ግንኙነት ላይ ማተኮር እንደምትፈልጉ አስቀድሞ መወሰን።
3. በርዕሰ ጉዳዩ (ይሁዲነት፣ እስራኤል፣ የዓለም ይሁዲ ወይም የእስራኤል ይሁዲ) መሰረት ለዳዊት ኮከብ የምንሰጠውን ትርጉም መወሰን።
4. እያንዳንዱ ንድፍ ድንገተኛ መደነቅን እንዲፈጥር እና ሃሳብን እንዲያጭር ንድፎቹን ገልጾ ከማሳየት በፊት የተመረጠውን ምልክት ቀድሞ መተንተን ያስፈልጋል።
5. ካርታዎቹ የሚሰጡት ትርጉም ከተወሰነ በኋላ ወለል ላይ ፊታቸውን ወደላይ እንዲታይ አድርጎ መደርደር ወይም ሁሉም ሰው በሚያይበት መልኩ ግድግዳ ላይ መለጠፍ ይቻላል።
6. ጥልቅ ውይይቶችን ለማጫር ካርታዎቹን ከ3-5 ሰዎች ባሉበት ወይም ከዚያ ሰፋ ባለ ቡድን ይጠቀሟቸው።

የሚከተለው ምሳሌ የካርታዎቹ ስብስብ “ይሁዲነት እና እኔ” በሚል ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ከይሁዲ ታዳጊ ወጣቶች ጋር የተደረገ ውይይትን የሚያሳይ ነው። መምህሩ ውይይቱን በዚህ መልክ ሊመራ ይቻላል፡-

- ለሚቀጥሉት 30 ደቂቃዎች እያንዳንዳችን ስለይሁዲ ማንነታችን የሚሰማንን ስሜት እና የግል ዕይታችንን እንድናጤን ሁላችሁንም እጋብዛለሁ።
- አሁን የማሳያችሁ ካርታዎች ላይ ያሉት እያንዳንዳቸው ንድፎች አንድ ሰው በዳዊት ኮከብ ከሚመሰለው የይሁዲ ማንነቱ ጋር ያለውን ትስስር የሚመለከትበትን ልዩ ልዩ መንገዶች ይወክላሉ።
- ተማሪዎቹ ክብ ሰርተው በተቀመጡበት፣ መምህሩ ካርታዎቹን እንዲታዩ አድርጎ በክቡ ውስጥ ዙሪያውን ይደረድራቸዋል።
- መምህሩ በመቀጠል - ከፊት ለፊታችሁ የሚገኙትን ንድፎች ጥቂት ደቂቃዎችን ወስዳችሁ አጢኑ፣ እያንዳንዱ ካርታ ምን እንደሚወክል አስቡ፥ በመቀጠልም ለራሳችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቁ - ይላል። እያንዳንዱ ካርታ ምንን ይወክላል? እነዚህን የተለያዩ ግንኙነቶች ከይሁዲ ማንነት ጋር እንዴት ታዛምዷቸዋላችሁ?

**በእያንዳንዱ ውይይት ውስጥ ልንጠቀማቸው የምንችላቸው የተወሰኑ የመንደርደሪያ ሀሳቦች ከዚህ በታች በምሳሌነት ቀርበዋል፡-**

1. በአሁኑ ወቅት ስላላችሁ የይሁዲ ማንነት አስቡ። በአሁኑ ወቅት ይሁዲ መሆን ማለት ለእናንተ ምን ማለት ነው? የትኛው ካርታ ነው የእናንተን ስሜት የሚወክለው? እባካችሁ ካርታውን መርጣችሁ በማንሳት የሚሰማችሁን ስሜት ለቡድኑ አባላት አካፍሉ።
2. ከእናንተ ተሞክሮ ተቃራኒ የሆነን ከይሁዲነት ጋር ያለ ዝምድናን የሚወክል ካርታን ምረጡ። ይህንን ካርታ እና ለምን እንደመረጣችሁት አስረዱ።
3. ከይሁዲነት ጋር የነበራችሁን ነገር ግን አሁን የተቀየረ ግንኙነት የሚያሳይ ካርታን ፈልጉ። ይህ ግንኙነት እንዴት ሊቀየር እንደቻለ ወይም እንዴት በጊዜ ሂደት እየተለወጠ እንደመጣ አስረዱ።
4. የቀረቡትን የተለያዩ ካርታዎች ተመልከቱ። የትኞቹ ካርታዎች ጠንካራ የሆነ ትዝታን ይጭሩባችኋል? እስቲ አካፍሉን።

5. የቀረቡትን የተለያዩ ካርታዎች ተመልከቱ። የትኞቹ ካርታዎች ጠንካራ የሆነ ስሜት ይቀሰቅሱባችኋል? እስቲ አካፍሉን።
6. በእነዚህ ንድፎች ያልተወከሉ ዕይታዎች ወይም ተሞክሮዎች ያሉ ይመስላችኋል? ምን ወይም ማን አልተወከለም ብላችሁ ታስባላችሁ? ይህንን የካርታዎች ስብስብ የተሟላ ለማድረግ ምን የምትጨምሩት ነገር አለ?

**ውይይቱ ግቡን መቷል ብላችሁ ታስባላችሁ?** ሌላ የማተኮሪያ ርዕሰ ጉዳይ በመምረጥ እና ከላይ የተገለጹትን መመሪያዎች በመድገም ውይይቱን "ዳግም አስጀምሩት"።

ለምሳሌ ካርታዎቹን ሰብስቡ እና በድጋሚ ወለሉ ላይ በማስቀመጥ እንዲህ በሉ፡- "አሁን ደግሞ ከፊት ለፊታችሁ የሚገኙት ካርታዎች **ከእስራኤል ጋር ያላችሁን ግንኙነት** (ከይሁዲነት አይደለም) እንዴት እንደሚወክሉ አስረዱ። ንድፎቹን በድጋሚ በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሳችሁን ጠይቁ- ከእስራኤል ጋር ያለኝን ግንኙነት እንዴት አየዋለሁ? ስለእስራኤል ሳስብ ከሚከተሉት ንድፎች ውስጥ የትኞቹ ሃሳቤን የበለጠ ይገልጹልኛል?"

ተሳታፊዎቹ አዳዲስ ካርታዎችን እንዲመርጡ እና ውይይቱን ዳግም እንዲጀምሩ ጠይቁ። በመቀጠልም ከላይ የቀረቡት የመንደርደሪያ ሃሳቦች በይሁዲነት ፋንታ እስራኤልን እንዲወክሉ አስተካክሏቸው።

## ተጨማሪ ትምህርታዊ ነጥቦች

*ቺካጎ ከሚገኘው አይሴንተር (iCenter) ትምህርቶች የተወሰደ*

1. ካርዶቹ ተማሪ ተኮር ተሞክሮዎችን ለማበረታታት የታለሙ ናቸው - ይህ ልምምድ ለተማሪዎች አስተያየታቸውን፣ ሃሳባቸውን እንዲሁም ስሜታቸውን ለመግለጽ የተሰጣቸውን አጋጣሚ አጋጣሚ እንዲጠቀሙ ለማስቻል የተዘጋጀ ሲሆን ዋና ተዋናዮቹ ተማሪዎች ናቸው።
2. ተሳታፊዎች የራሳቸው ታሪክ ባለቤቶች እንዲሆኑ እና በራሳቸው የይሁዲነት ጉዞ ውስጥ ራሳቸው መሪ እንዲሆኑ ዕድል ስጧቸው።
3. ይህንን ውይይት ስታደርጉ የተሳካ የሃሳብ ልውውጥን ለማድረግ ያስችል ዘንድ ድህንነቱ የተጠበቀ እና አስተማማኝ ሁኔታ ፍጠሩ። ተሳታፊዎች የሌሎችን ሃሳብ በማክበር እና ለውይይት ክፍት በሆነ መልኩ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ አበረታቱ።
4. በተሳታፊዎች እና በተወሰኑ ንድፎች መካከል በሚኖሩ አወንታዊ ስሜቶች እና ግንኙነቶች ላይ ብቻ አታተኩሩ። ተሳታፊዎች ቅሬታን በሚፈጥርባቸው ወይም ምቾት በሚነሳቸው ንድፍ ዙሪያ የሚሰማቸውን ስሜት እና ሃሳባቸውን እንዲገልጹ አበረታቱ - *"ከምቾት ክልላችን ስንወጣ ለማደግ ምቹ አጋጣሚን እናገኛለን። በተለይም ስለእስራኤል ስናወራ ምቾት የሚነሱንን ስሜቶች ለመቀበል ምቾት ሊሰማን ይገባል"* (ዶ/ር ዘሃር ራቪቭ)።

## ለፕሮግራሙ ማጠቃለያ የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ከአንደኛው ግንኙነት ወደ ሌላኛው ግንኙነት ስንሸጋገር (ለምሳሌ - ስለ ይሁዲ ማንነታችን ከመወያየት ከእስራኤል ጋር ስላለን ግንኙነት ወደ መወያየት ስንሸጋገር) እያንዳንዳችሁ የውይይታችን ርዕስ ከነበረው ጉዳይ ጋር የነበራችሁ ትስስር በምን መልኩ ተለየ? በእነዚህ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንደቡድን የሚሰማንን ስሜት በተመለከተ ልንለው የምንችለው ነገር አለ?
2. ከአንደኛው ርዕሰ ጉዳይ ወደ ሌላኛው ርዕሰ ጉዳይ ስንሸጋገር ሙሉ በሙሉ የትርጉም ለውጥ ያመጣባችሁ ንድፍ አለ? እስቲ ንገሩን።
3. የተለያዩ ንድፎችን አስመልክቶ ጓደኞቻችሁ ሃሳባቸውን ወይም ስሜታቸውን በሚገልጹበት ጊዜ የወሰዳችሁት ትምህርት ወይም አዲስ ያገኛችሁት መረጃ ወይም ዕይታ አለ?
4. ዛሬ በሰማችኋቸው ነገሮች የተነሳ በእናንተ ውስጥ የተቀየረ ነገር አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?

## ተጨማሪ የአጠቃቀም መንገዶች

1. **<u>በሥነ-ጥበብ</u>** - ልምምዱን እየሰራችሁ እንዳለ፣ ተሳታፊዎች ለዳዊት ካርዶች ራሳቸው በሚሰጧቸው ትርጓሜዎች መሰረት የራሳቸውን ንድፍ እንዲስሉ ባዶ ወረቀት ልትሰጧቸው ትችላላችሁ። ተሳታፊዎች የፈጠራ ስራቸውን ለክፍሉ እንዲያጋሩ ጠይቁ።
2. ***<u>ታሪክ በመንገር</u>*** - ተሳታፊዎችን በቡድን ከፍላችሁ ለእያንዳንዱ ቡድን ከ4-6 ካርታዎችን ስጡ። ተሳታፊዎች ስለእስራኤልም ሆነ ስለይሁዲነት (እዚያው የፈጠሩትን ታሪክ) በታሪክ መልክ እንዲያካፍሉ እና የተሰጧቸው እያንዳንዳቸው ካርታዎች የሚወክሉትን ገጸ-ባህሪ በታሪክ ውስጥ በማካተት እንዲተርኩ አድርጉ። ተሳታፊዎቹ የቡድናቸውን ታሪክ ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ አበረታቱ።
3. **<u>ካርታዎቹን አንድ በአንድ በመስጠት -</u>** ከ10 በታች የሆኑ ተሳታፊዎች ያሉበት አነስተኛ ቡድን ውስጥ፣ የካርታዎቹን አጠቃቀም በተወሰነ መልኩ ልትለውጡ ትችላላችሁ። “ካርታዎቹን አንድ በአንድ በመስጠት” ተሳታፊዎቹን “እዚህ ካርታ ላይ ምን ይታያችኋል?” እያላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ። ይህም እያንዳንዱ ሰው እያንዳንዱን ካርታ እንዴት በተለያየ መልኩ እንደሚተረጉም ለማሳየት ጠቃሚ መንገድ ነው።

## ምስጋና እና ተጨማሪ መረጃ

በይሁዲነት እና በእስራኤላዊነት ዙሪያ ያሉ ውስብስብ ግንኙነቶችን በንድፎቿ አማካኝነት በጥበብ፣ በጥንቃቄ፣ እና በጥልቀት ስለገለጸቻቸው፣ ለእስራኤላዊቷ የሥነ-ጥበብ ባለሙያ ሳፒር ዊነር አቪቭ ታላቅ ምስጋናን አቀርባለሁ።

የይሁዲ ለእስራኤል ኤጀንሲ (JAFI) እና የእስራኤልን እና የዓለም ይሁዲዎችን ትስስር ማጠናከሪያ ብሄራዊ ጥምረት (AMI) ለዚህ ፖሮጀክት ላደረጉት ድጋፍ አመሰግናለሁ። የዚህ ፕሮጀክት የመጀመሪያው ስሪት በግድግዳዎቻቸው ላይ ለዋሉት የዴንቨር ይሁዲ ማህበረሰብ እና የኮሎራዶ ይሁዲ ማህበረስብ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

**ሳፒር ዊነር አቪቭን** በዚህ የኢሜይል አድራሻ ማግኘት ትችላላችሁ፡- sapirwin@gmail.com

## የዳዊት ካርታዎች ፈጣሪ ዮኒ አሎን



ዮኒ አሎን በእስራኤል እና በይሁዲ የትምህርት ዘርፍ በፈጠራ የታገዙ የትምህርት መርጃዎችን በመፍጠር በእስራኤላዊ እና እስራኤላዊ ባልሆኑ ይሁዲዎች መካከል ትስስር ለመፍጠር የሚሰራ ባለሙያ ነው። እ.አ.አ. ከ2013-2015 በዴንቨር የይሁዲ ማህበረሰብ የይሁዲ ኤጀንሲ የእስራኤል ቃል-አቀባይ የነበረ ሲሆን፣ ከዚያ አስቀድሞ ለሰባት ዓመት ተኩል በእስራኤል መከላከያ ኃይል ውስጥ (በMaj res. ማዕረግ) አገልግሏል። በውትድርና አገልግሎት ዘመኑ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ የሰራ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል በእስራኤል መከላከያ ኃይል የዓለም አቀፍ ትብብር ክፍል ውስጥ በተጠሪ መኮንንነት አገልግሏል። ከ2017 ጀምሮ ከበርካታ የይሁዲ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የትምህርት ዘርፍ ፕሮጀክቶች ላይ በግሉ በአማካሪነት ይሰራል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ ጥያቄ እና ምክሮች፣ ወይም ለእርስዎም ሆነ ለመምህራኖችዎ በኢንተርኔት የቀጥታ የድጋፍ ጥሪ ጥያቄን ለማቅረብ፣ **ዮኒ አሎንን** በዚህ የኢሜይል አድራሻ ያግኙ፡- **creativealon@gmail.com**

ከፌብሩዋሪ 2025 ጀምሮ፣ ይህንን ሰነድ በሚከተሉት ቋንቋዎች በፒዲኤፍ ፋይል ማግኘት ይቻላል፡- እብራይስጥ፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ስፔንኛ፣ ራሺያኛ፣ ጀርመንኛ፣ ዩክሬንኛ፣ ፖላንድኛ፣ እና አማርኛ።

ድረ ገጻችንን ለመጎብኘት:- https://www.yonialon.com/david-cards

የበለጠ ለማወቅ ይህንን QR ኮድ ስካን ያድርጉ።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው – ዮናታን (ዮኒ) አሎን/ 2025